## ለአቶ ግርማ ካሳ ፣

# “የካቲት 12-እንጀራ ወይንስ ጊንጥ”
# ላይ የቀረበ ትችት

## ከዘለቀ ሃብተየስ

አቶ ግርማ ካሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያስነበቡን መጣጥፎቾ ምክንያት ሆነውን ካወቅኖት የአገሮ ልጆች አንዱ ነኝ። ዛሬ ዛሬ ከቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴ ተገንጥሎ ለወጣውና እራሱን “የቅንጅት አለምአቀፍ አመራር” ብሎ ለሚጠራው ቡድን የቀኝ እጅ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ሆነዋል፡፡ መጣጥፎችን ላነበበ ሰው ለምን ከነብርሃነ መዋ ወገን እንደቆሙ ለማወቅ አይቸገርም። እኔ በዚያ ወገን ካላችሁት ውስጥ ለእርሶ ከፍ ያለ አክብሮት አለኝ። ምክንያቱም እምነቶን ሳይሸሽጉ ስለሚነግሩን ነው። በዚች አጭር ጽሑፌ የማተኩረው “የካቲት 12 -እንጀራ ወይንስ ጊንጥ” በሚል ርእስ ባስነበቡን መጣጥፍ መልእክት ላይ ነው።

“የካቲት 12-እንጀራ ወይንስ ጊንጥ”ን ወድጄዋለሁ። መውደዴ ታዲያ በጽሑፎ ጭብጥ በመስማማት ሳይሆን እምነቶን በግልጽ ስላሳዩን ነው። በዚህም እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ የእርሶና የሚደግፉአቸው የእነ አቶ ብርሃነ መዋ በቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ውስጥ የፈጠራችሁት ልዩነት መነሻ መሰረት (motive behind) ምን እንደሆነ በግልጽ ቋንቋ አሳይተውናል። አቶ ግርማ በዚህ ጽሑፎ ላይ የግንቦት 97 “ምርጫን” ተከትሎ ወያኔ (እርሶ መንግስት ወይም ኢህአዴግ ማለት ይመርጣሉ) የወሰዳቸው እርምጃዎች እንዳስቆጣዎትና ይህም ሁኔታ ከእንቅልፎ እንደቀሰቀሰዎት ገልጸው ሆኖም ግን ዛሬም ድረስ ለወያኔ መንግስት ያሎዎትን ክብር እንዲህ ሲሉ ነግረውናል (ገጽ 1)

> ኢህአዴግ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲስፋፋ ትልቅ አሰተዋጸ ማድረጉን ማንም የሚክደው ሐቅ አይደለም ፣...ኢህአዴግ ለዚህ ዴሞክራሲያዊ አስተዋፃዎቹ ሊመሰገን ይገባል፡፡

አቶ ግርማ ተሳስተዋል፡፡ ይልቁንም ወያኔ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ ማስፋፋቱን ማንም የሚቀበለው ሀቅ አይደለም፡፡ ወያኔ መቼ ነው ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ያስፋፋው? የዴሞክራሲ ፍቺው (ምሰሶው) እኮ ስልጣነ-ሕዝብ ማለት ነው። ዴሞክራሲ እርሶ እንዳሉት በኢትዮጵያ ተስፋፋ ሳይሆን ጀመረ የምንለው መንግስት በህዝብ ነጻ ምርጫ በአብላጫ ድምጽ ሲመሰረት ነው ፤ የሥዩመ-እግዚአብሔርም ሆነ የሥዩመ-ተመንጃ ዘመን ተሽሮ የሥዩመ-ሕዝብ መንግስት ሲተከል ነው። እንጂማ ወያኔ እንዳደረገው በጠመንጃ ስልጣን ከያዘ በኌላ እኔ እንደ ደርግ አይደለሁም፣ ተቃውማችሁኝ ወሬ አወራችሁ ብዬ አልገድልም ፤ እናንተው የምታወሩ ሰዎች ተቀባብላችሁ በምታነቡት ጋዜጣ ወይም መጽሄት ላይ መጻፍም ትችላላችሁ፤ "ምርጫም" ውስጥ ግቡ፣ የተወሰነ የፓርላማ ወንበርም እመጸውታችኃለሁ (ለእናንተ ብዬ ሳይሆን በምድር እጸድቅ ብየ)፣ ነገር ግን የጽድቅ ስልጣኔን የሚያሰጋ ነገር ውስጥ ከገባችሁ ግን አይማረኝ ብምራችሁ ማለቱ ወያኔን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ አስፋፋ አያሰኘውም። ያደረገውም እያደረገ ያለውም ይሄንኑ ነው።

አቶ ግርማ በጽሑፎ በግልጽ ያስቀመጡት ሌላው ነጥብ ወያኔን አገዛዝህን አስተካክለህ ከስህተትም ታርመህ ግዛን ነው (ገጽ 2)

> ኢትዮጵያ ውሰጥ የታዩት አንጻራዊ የኢኮኖሚ መሻሻሎች፣ የተገነቡት አዳዲስ ትምህርት ቤቶችና መንገዶች፣ በኢህአዴግ የተሾሙት የቀድሞ የመዲናችን ከንቲባ ክቡር አቶ እርከበ እቁባይ ባአዲስ አበባ ከተማ ያሳዩት ተጨባጭና የሚታዩ ለውጦች… በአንዳንዶቻችን ዘንድ ለኢህአዴግ መጠነኛ ከበሬታ እንዲኖረን አድርጎን ነበር

ለአቶ ግርማ ችግራችን ኢኮኖሚያዊ ብቻ ነው፡፡ወያኔ የሚፈጽመውም ሰብአዊ ስህተት ነው፡፡ አቶ ግርማ፣ ድህነታችን የአምባገነናዊ ስርዓትና የድህነት የሁሌም ተዛምዶ (አብሮ የመገኘት) ውጤት እንጂ በወያኔ ላይ ላለን መሰረታዊ ቅራኔ መነሻ ምክንያት አያደለም፡፡ የቅራኔያችንን ምንጭና የትግላችንን መነሻ ምክንያት መሪያችን የሆነችው ብርቱካን ሚደቅሳ "ሰው ያለነጻነቱ ምን ሰው ነው?" ብላናለች፡፡ እውነት ነው፣ ሰው (በአገሩ ላይ) ያለነጻነቱ ምን ሰው ነው!

ሌላው አቶ ግርማ ያደረጉትም ሆነ ከነ አቶ ብርሃነ የሚደመጠው በእስር ቤት ያሉ መሪዎቻችንን ስም ከፍ አድርጎ ማወደስ ነው። ዓላማው ግልጽ ይመስለኛል። አንድም መሪዎቻችን በወያኔ የአፈና እስር ቤት ውስጥ እስካሉ ድረስ በሚደረገው ነገር ላይ ሁሉ ግልጽ መልስ መስጠት ስለማይችሉ እነ ብርሃነ የሚናገሩትን ለምንሰማና የጻፉትን ለምናነብ ግን የመሪዎቻችን መልእክተኛና የእነሱ ዐላማ አራማጆች ሆኖ ለመታየት ነው። ከዚያም በላይ ምናልባትም መሪዎቹ ውዳሴውን ሲሰሙት (መስማታቸው አይቀርም) ይማርካቸውና እነ ብርሃነን ከድርጊታቸው እነዲታቀቡ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ምላሳቸውን ይይዘዋል ከሚል ብልጣብልጥነትም ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

ለምሳሌ አቶ ግርማ "አንዳንድ በውጭ አገር ያሉ ቅንጅትን የማይወክሉ ቅንጅት ነን ባዮች የኢህአዴግ መሪዎችን ለይተው በጨዋ ቋንቋ በመውቀስ ፈንታ አራዊት ብለው ይሳደባሉ..." (ገጽ 4) በማለት ምሬቶን ገልጸው ፣ ፕሮፌሰር መስፍንን ግን "የኢትዮጵያውያን ሁሉ አባት" በማለት ውዳሴ ይቸራሉ። አዎ ፕሮፌሰር መስፍን ህይዎታቸውን ሙሉ ለአገራቸው በሰሩት ሥራና ዛሬም አካላቸው በደከመበትና ጉልበታቸው በዛለበት ወቅት እየከፈሉ ያሉት መስዋዕትነት በመሬት ላይ የሚቆም የድንጋይና የብረት መታሰቢያ ሳይሆን በእያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ የታተመ ሃውልት አኑረዋል። ግን እኮ አቶ ግርማ፣ መስፍን በተደጋጋሚ ወያኔንና የአስተዳደር ስርዓቱን "የህገ -አራዊት ስርዓት" ብለው ነቅፈዋል። በ97 የ "ምርጫ" ክርክር መድረክ ላይ መስፍን የወያኔን ሕገ-መንግስት "ከተጻፈበት ወረቀትና ቀለም የበለጠ ዋጋ የለውም" ብለው ሀቁን የተናገሩ ጀግና ናቸው። ታዲያ መስፍንን አወድሶ ሌሎችን መክሰስ ለሌላ ነው። ከላይ ካነሳኃቸው ከሁለቱ ባንዱ ወይም በሁለቱም ምክንያት መሆን አለበት። አለዚያማ ማንም ለኢትዮጵያ ነጻነት የቆመ ወገን የወያኔን ማንነት ሲያጋልጥ አበጀህ እንጂ አጠፋህ አይበልም፡፡

እኔ እንደሚመስለኝ አቶ ግርማ ንጹህ እምነቶን ነው የሚነግሩን፡፡ እርሶ እንደሚሉን ግን ወያኔን እንዳናባብል በማባበል ከህዝብ የታረቀ አምባገን (ለዚያውም እንደወያኔ አይነት ፍጹም ዘረኛና አምባገነን) መንግስት ከታሪክ አልጠቀሱልንም፡፡ ይልቁንም ያስነበቡን የንጉስ ሮብዓም ታሪክ ያምባገነኖች ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ አቶ

ግርማ ከነአቶ ብርሃነ የሚመሳሰሉት ለወያኔ ባሎት ገራገር ልብ ብቻ ነው፡፡ ተግባራችሁ ግን ለየቅል ነው፡፡

እነ አቶ ብርሃነ ምስጢራቸውን ደብቀውን ዋና ጸረ- ወያኔ ታጋይ ሆነው ለመታየት ይራወጣሉ፡፡ ወያኔ ስህተቱን አርሞ ይግዛን የሚሉ ሰዎች ስብስብ ሻለቃ ዮሴፍ "አፍቃሪ ወያኔ ለሆነ ድረ- ገጽ መግለጫ ሰጡ" ብሎ በመጮህ ሻለቃውንና የድርጅቱን አመራሮች በወያኔነት ለመክሰስ መዳዳትን ምን አመጣው? ለምን ገንዘቡን በመስጠት ትግሉን የሚያግዘውን ህዝብ በሚያስደነግጥ "የገንዘብ ተሰረቀ" የፈጠራ ክስ ውስጥ ገባችሁ? ለምን አስቀድማችሁ በቀጥታ "እነ ሻለቃ አክራሪዎች ናቸው ፣ እኛ ግን ከወያኔ ጋር መደራደር የሚያስችል የሰለጠነ ፖለቲካ አራማጆች ነን" አትሉንም ነበር?

የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅ መስዋዕትነት የከፈለበትን ደርጅት በማዳከምና በመሰንጠቅ ላደረሳችሁት ጥፋት ፍርዱን ከታሪክ ፣ ከህዝብና ከእግዚአብሄር ታገኙታላችሁ፡፡ ኢትዮጵያ ከዚህ አሳፋሪ የክህደት ድግግሞሽ የምትወጣበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም፡፡ የሚሆነው ሁሉ ሊነጋ ሲል እንደሚጨልመው ነው፡፡

You can reach the author: zelekehab@yahoo.com